# አባቴ ያቺን ሰዓት




"...በፍርሐት ተይዞ የነበረው ጦር ከየምሽጉ እየወጣ ማጥቃት ጀመረ። ሞራሉ ተገንብቶ ካላጠቃሁ ካልተዋጋሁ ማለት ጀመረ። ጄ/ደምሴ ወደኛ ዞር አሉና "ይሄ ተራ ሽፍታ ነበር ሠራዊቱን አስጨንቆ የነበረው። ወንበዴው አይደለም። እናንተ ናችሁ ሠራዊቱን ፈሪ ያደረጋችሁት። የመሪ እንጂ የተመሪ ፈሪ የለውም!" አሉ። ከሞሰቦ አካባቢ ማጥቃቱ ቀጥሎ በተከታታይ ያለሚቋረጥ እያጠቃ የኢትዮጵያ ጦር ውቅሮን ተቆጣጠረ። እንደገና በመቀጠል የወያኔን ጦር ማጥቃት ቀጠለ....።"

"..ብ/ጄ ታሪኩ አይኔ ላይ...የተደረገው ያሳዝናል አድሚ ልኩን ጦር ሜዳ ኖሮ... ተይኝ እባክሽ፣ ሰሞኑን ደግሞ ሲቪል ሆነው ለዓመታት ሲሠሩ የነበሩትን እያነሱ የጦር አዛዥ ማድረግ ሆኖአል ሥራቸው። ዘለቀ በየነ በሜ/ጄኔራልነት የደቡብ ዕዝ አዛዥ ሆኗል። ይሄ ማነው ውብሸት ደሴ በሻለቃነት ወደ ሲቪል ተቀይሮ የፖለቲካ ሥራ ሲሠራ የኖረ ነው። አሁን ከ15 እስከ 20 ዓመት ልምድ የሚጠይቀውን ቦታ

ያውም ሶስት ደረጃ ዘሎ በሜ/ጀኔራልነት የምሥራቅ ዕዝ አዛዥ… ምን ትይዋለሽ ታዲያ ይሄንን፣ ቀልድ አይደለም?”

ጀ/መርዕድ የሚናገረውን ማመን እንዳቃተው የፈጠጡት ዐይኖቹና ወደ ጎንና ወደ ጎን የሚዘዋወረው ጭንቅላቱ ይገልፃሉ።…”

….አባቴ “ወርቁ ይህ ሁኔታ እስከመቼ ነው በዚህ መልክ የሚቀጥለው? መሠረታዊ ለውጥ ካልተደረገ ይች አገር ከፍተኛ አደጋ ላይ ነው የምትወድቀው” ብሎ ሲጀምር ፣ ጀ/ወርቁ ወዲያው ተቀብለው “ጀነራል እኛ እኮ ለህዝብ የተሻለ ሥርዓት እናመጣለን ብለን እንጂ፣ የአንድ ሰው አምባገነን መንግሥት ለመመስረት አልነበረም ለውጡን የደገፍነው” አሉ። የፖለቲካ ኃላፊ እንደዚህ ሲናገር ሰምቼ ስለማላውቅ ግራ ገባኝ። ይህ ሰው ተናግሮ ለማናገር ፈልጎ ቢሆንስ?...

….በመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጊዜ፣ መንግሥቱ ከወረደና ሻዕቢያ የተወሰነ ሥልጣን እስከተሰጠው ድረስ፣ የኤርትራን ነጻነት ጥያቄ ለማንሳት ዝግጁ እንደነበር ገልጸዋል። እንዳውም ሻዕቢያ አስመራ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ እየተካሄደ ወደ ሕወሐት (TPLF) መልእክት እንደላከ እና መልዕክቱም በፍጥነት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራውን እንድንደግፍና ከአስመራ ከእኛ ጋር ለመገናኘት የሚላኩትን የመፈንቅለ መንግሥት አድራጊ ቡድን ወኪሎችን በአዲቃላ በኩል እንድንቀበላቸው የሚጠይቅ ነበር ብለዋል። ሕወሐት ግን ይህን ጥሪ እንዳልተቀበለውና ውሳኔውን በራሱ ሬዲዮ ሲገልጽ፣ የሻዕቢያ አመራር በውሳኔው ማዘናቸውን ገልጸዋል…። ከአባቴ ያችን ሰአት መጽሀፍ የተወሰዱ

*አባቴ ያቺን ሰአት ደረጀ ደምሴ ስለ አባቱ ሜ/ጀ ደምሴ ቡልቶ፡ በኢትዮጵያ ሰራዊት ውስጥ በአመራር ላይ ስለነበሩት ከፍተኛ መኮንኖች፤ እንዲሁም ስለ ግንቦት 81 መፈንቅለ መንግስት የጻፈው መጽሃፍ ነው። ደረጀ ከአባቱ ጋር በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወረ ያየውን እና በቦታው ከነበሩ የተለያዩ ከፍተኛ መኮንኖች ያጠናቀረውን፤ በጣፋጭ ትረካ አቅርቦታል።*

በአቀራራቡ ልዩ የሆነው ትረካ ከዚህ በፊት ተደብቀው የነበሩ ምስጢሮችን የያዘ ብቻ ሳይሆን፤ በኢትዮጵያ ሠራዊት ውስጥ የነበሩትን ችግሮች ምን ነብሩ? የሌ/ኮ መንግስቱን ሥርዓት ለመጣል የተደረገው ሙከራ ሂደት እንዴት ነበር? የመፈንቅለ መንግስቱ መሪዎች ዓላማስ ምን ነበር? መነስኤዎቹስ ምንድናቸው? የኢትዮጵያ ሰራዊትና መሪዎቹ ያጋጠሙዋቸው ችግሮች በተለይም የፖለቲካ ሥርዓቱ በጦሩና በመሪዎቹ ላይ የፈጠራቸው ዘርፈ ብዙ መሰናክሎች ምን ይመስሉ ነበሩ? መፈንቅለ መንግስቱስ እንዴት ከሸፈ ? የመፈንቅለ መንግሥቱስ አሳዛኝ ፍጻሜ የአገራችንን እጣ ወዴት አመራው? ወዘተ… ብዙ አመታት በፈጀ ጥናት ፡ በርካታ ቃለ ምልልሶችና በጸሃፊው ገጠመኞች ተመስርቶ በሰፊው ይዳስሳል።

የመጽሃፉ አተራረክ በአባትና ልጅ ታሪክ ላይ የተመሰረት እና አንባቢን የሚስብ፡ ከገጽ ወደ ገጽ በጉጉት የሚያስተላልፍ፡ በአይነቱ ከዚህ በፊት ከወጡት መጻሕፍት የተለየ ነው። ከመጽሃፉ በስተጀርባ የተያያዘው የሜ/ጄ ደምሴ ቡልቶ የግል የጦር ሜዳ ማስታወሻ ነው። ከሐምሌ 29 1977 ዓም ጀምሮ እስከ ኅዳር 3 1978 ድረስ የባሬንቱን ከተማ ለማስለቀቅና ናቅፋን ለመቆጣጠር በተደረጉት ዘመቻዎች ግዜ ጀ/ደምሴ ቀን በቀን የያዙት ማስታወሻ በራሳቸው እጅ ጽሁፍ እንዳለ ለታሪክ ተመራማሪዎች እንዲያገለግል ደራሲው አቅርቦታል። *አባቴ ያቺን ሰአት ያንብቡ።*


Aesop Publishers & Distributors
T: 202-386-3037

*NOW AVAILABLE ON-LINE! To Buy "ABATE YACHIN SE'AT" on-line*
*Go to* *www.demissiebulto.com*